# መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ - መኢሶን -

# ALL ETHIOPIA SOCIALIST MOVEMENT (MEˊSONE)

## ቃለ መጠይቅ ከዶ/ር ነገደ ጎበዜ ጋር

<u>ያለፈውና መጭው ትግል</u>

፩ኛ. የወቅቱ የፖለቲካ ሂደት

፪ኛ. ቀይ ሽብር

፫ኛ. መኢሶን፤ ሶቭየቶችና ኢትዮጵያ በ 1969

፬ኛ. መኢሶን ተሸንፏል ? ከኢሕአፓ በምን ይለያል ?

<u>ለአንባቢዎች፤</u>- ይህ ቃለ መጠይቅ ቀደም ሲል በጦቢያ መጽሄት በቅጽ 2 ከቁጥር 11 እስከ 12 1986፤ በቅጽ 3 ከቁጥር 1 እስከ 3 1986 በተከታታይ የወጣ ሲሆን፤ ብዙ በውጭ የሚገኙ አምስቱንም ቁጥሮች ተሟለተው ያላገኙ አንባቢዎች ድርጅታችንን በየጊዜው ከመጠየቃቸውም በላይ፤ በበኩላችንም ይህ የቃለ መጠይቅ ጽሑፍ ለአንዳንድ ጉዳዮች የውይይት መነሻ የሚሆኑ ነጥቦችን ያስጨብጣል ብለን ስለገመትን፤ ጽሁፉን አሰባስበን በዚህ መልክ አቅርበነዋል።

መልካም ንባብ

1987

# ቀይ ሽብር

**ጥያቄ**፦የሽግግሩ መንግሥት የቀይ ሽብር ወንጀለኛ ነዎት ይላል:: ይቀበሉታል?

**ዘ.ቢስ**፦ይህንን ውንጀላ እኔም ድርጅቴም መኢሶን ጨርሶ አንቀበለውም:: ባለፉት 20 ዓመታት በኢትዮጵያ ብዙ እጅግ ብዙ ደም፣ ብዙ ለጅግ ብዙ እንባ ፈሷል፣ በተለያዩ ምክንያቶችና በተለያዩ ኃይሎች አማካኝነት:: በዚህ ወቅት ወንድም፣ እህት፣ እናት፣ አባት፣ ዘመድና ወዳጅ ያላጣ ቤተሰብ ያለ አይመስለኝም:: አሁንም በፖለቲካ ጉዳይ ዜጎች ይታሰራሉ፣ ይሞታሉ፣ እንባ ይፈሳል:: ከሁሉም ወገን የሞቱትና አሁንም የሚሞቱት ሰላሳ ይሁኑ አርባ፣ ሺህ ይሁኑ አስር ሺህ እንዲሁ ዝምብለው ስታቲስቲክስ አይደሉም:: እያንዳንዱ ለማለት እህት፣ ወንድም፣ እናት፣ አባት፣ ዘመድ ወዳጅ ያለው ዜጋ ነው:: ለተራዎቹ ሃዘንና እንባ እየተወ የሚያልፍ:: አንዲት እናት ልጇ በጦር ሜዳ ሞተ በከተማ፣ ከእስር ቤት ተጉትቶ ተረሸነ፣ ከመንገድ ላይ ተደፍቶ ይቅር፣ የኢትዮጵያን አንድነት ለማስከበር ከህወሃትና ከሻዕቢያ ሲተናነቅ አለፈ፣ ወይስ ኤርትራን ለማስገንጠል ከአጼ ኃይለ ስላሴና ከደርግ ወታደር ሲዋጋ ተሰዋ፣ በቀይ ሽብር ተሰለበ በነጭ ሽብር፣ ለሷ ይኸ ሁሉ በሁለተኛ ደረጃ የሚመጣ ጉዳይ ነሁ:: ልጇን አጥታለች:: እሷ የምታየው ይኸንን ነው::

ባለፉት 20 ዓመታት ስለደረሰው አሰቃቂ ሲነሳ ለተሰውትም ለቀሩትም ከበሬታን በማይነሳ ጥሞና መሆን አለበት:: እንዲህ ዓይነቱ አስከፊ ዘመን በታሪካችን እንደገና እንዳይመጣ ምን እናድርግ? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ መሆን አለበት:: ካለፈው ትምህርት ለመቅሰም መሆን አለበት:: የፖለቲካ ንግድ ማካሄጃ ማድረግ ግን እጅግ አስጠያፊና የሚዘገንን ተግባር ሆኖ ነው የማየው:: የተሰውትን ሁለተኛ እንደመግደል:: ቀሪውን ዘመድ አዝማድ እንደገና ለሐዘንና ለሰቆቃ መጋበዝ ነው::

ከፍ ብዬ እንዳልኩት ባለፉት ዘመናት ሕይወታቸው ያለፈው ዜጎች እናቶች ልጆቻቸው በዚህ ዓላማ ይሙቱ በዚያኛው ደንታቸው አይደለም:: አንድ እናት ልጇ በመኢሶን ሥር ተሰልፎ ተሰዋ ግሩም ነው፣ በኢህአፓ ባንዲራ ስር ተሰዋ ጀግና ነው፣ ለአልባንያ ኮሙኒዝም ዓይነት ተዋደቀልኝ ቆራጥ ኢብዮታዊ ነው፣ በደርግ ባንዲራ ስር ሞተ ያበለው ከሃዲ ነው አትልም:: ያለፉትንም የቀሩትንም ማክበር ማለት ሁሉንም በአንድ ዓይን ማየት ማለት ነው:: ቀጥሎም ይህ ሁሉ ዜጋ መሰዋቱ አስፈላጊ ነበር ወይ? ብሎ መጠየቅ ይገባል:: ይህ ሰማዕትነት ደግሞ የትም ባክና እንዳይቀር ትምህርት መቅሰም ያስፈልጋል::



በኢትዮጵያ ካሉ የፖለቲካ ኃይሎች ሁሉ እንደዚህ ዓይነቱን የራስ ምርምር ሂደት መጀመርና ማካሄድ ያለበት አንድ ኃይል ቢኖር ህወሃት ነው ብዬ አምናለሁ::ከጅምሩ በአመጽ የተጸነሰ ኃይል ነው:: በጦር ሜዳ ሆነ በከተሞች በጅምላ ሆነ በግለሰብ ግድያ ሌሎች ዜጎችን እየገደለ፣ የራሱንም ታጋዮች እየሰዋ እዚህ የደረሰ ኃይል ነው፣ ከሱም ሆነ ከ«ጠላት» ወገን በሙቶ ሺህ የሚቆጠር ዘመድ አዝማድ እንባ ባህር እየዋኘ:: ያውም እንግዲህ ለዚህ እጅግ አጠራጣሪ ለሆነ ውጤት:: የህወሃት የአመጽ ሂደት የጦር ሜዳ የአልሞት ባይ ተጋዳይነት ሂደት ብቻ አይደለም:: እንደደርግ ወታደሮች እሱም ከተሞችንና መንደሮችን ሲይዝ «የጠላት ተባባሪ» እያለ አያሌ ሰዎችን ረሽኗል:: የህወሃት መሪዎች ገና ወደፊት ዝርዝሩ ሲወጣ የሚያፍሩበት ታሪክ አላቸው:: በዛው በድርጅታቸው ውስጥ እንኳ ተቃዋሚዎቻቸውን እያሰሩ፣ እየረሸኑ ነው የመጡት:: ከጥቂት ዓመታት በፊት የቀድሞ የህወሃት መሥራች አባል የነበረ አቶ ገብረመድህን የተባለ ታጋይ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የዛሬዎቹን የመንግሥት ቀንደኛ ባለሥልጣናት ስም እየጠራ እንዴት «የትግራይ ነጻ አውጭ ግንባር ተብሎ ይታወቅ የነበረውን የህወሃት ጣውንት ድርጅት «የእርቅ ድርድር» በሚል ሰበብ ጋብዘው በተኙበት . . . እንደጨረሷቸው የሰጠውን ሐተታ ተመልክቻለሁ:: ይህ የጦር ሜዳ የአልሞት ባይ ተጋዳይነት ድርጊት አልነበረም:: ተራ የነፍስ ግድያ ወንጀል ነበር:: ዛሬ እነሱ የበላይነት ይዘው ያውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከነሱ በተሻለ የሚያውቀውንና እንባ እስኪያልቅበት ያለቀሰበትን የደርግ ግፍ እንደ አዲስ ነገር በጋዜጣም በቴሌቪዥንም ሊነግሩበት ሲሞክሩ ታዝበናል:: ነገ ደግሞ ሌላ ኃይል የበላይነትን ሲያገኝ በድርጅትነት ብቻ ሳይሆን አብዛኞቹ የህወሃትና ኢህአዴግ መሪዎች በነፍስ ወከፍ የፈጸሙት ግፍ ይፋ እንደሚወጣ ቅንጣት አልጠራጠርም::

ለዚህ ነው በዚህ ጉዳይ እነ አቶ መለስ ዜናዊ አፍ አለን ብለው ሌሎችን ለመወንጀል ሲሞክሩ ለነሱ አፍራለሁ የምለው:: ዛሬ በሀገራችን ከኩለኔል መንግሥቱ አገዛዝ ቀጥሎ በምንም ምክንያት ይሁን በምንም ለዚህ የአመጽ ሂደት ዋና ተጠያቂ የሆነው ኃይል፣ እንደ ድርጅት ከሁሉ ባነሰ በአመጽ ውስጥ የተሳተፈውን ድርጅታችንን በሀገራችን ለተካሄደው አመጽ ተጠያቂ አድርጎ ለማቅረብ ሲሞክር በጣም ይዘገንነኛል::

እርግጥ መኢሶንን በቀይ ሽብር የሚወነጅለው ኢህአዴግ ብቻ አይደለም:: ብዙ ዜጎች አሉ:: አንዳንዶቹ ባለማወቅ፣ በመወናበድ፣ በቅንነት፣ ሌሎቹ ሆን ብለው፣ ነገሩን በሚገባ እያወቁት:: ሌሎች ደግሞ ኃላፊነትን ከራስ ለማውረድ:: የኢህአዴግ ከዚህ ሁሉ የሚለይበት አለ:: መጀመሪያ ከሁሉ አመጸኛና ግፈኛ የሆነው ድርጅት፣ ያለፈው አልበቃ ብሎት አሁንም በዚሁ በአመጽ የተሰማራ ድርጅት፣ ከሁሉ ካነሰ በአመጽ ሂደት የተሳተፈውን መኢሶንን፣ ዛሬ የሚካሄድ ሁኔታ ሳይሆን የዛሬ አሥራ ሰባት ዓመት ተፈጸመ በተባለ ወንጀል እፋረዳለሁ ሲል ቢያንስ ቢያንስ አስቀድሞ ራሱን መገምገም ነበረበት:: ሁለተኛ እነዚህ ሰዎች ሥልጣን ሊይዙ ጥቂት ወራት እስኪቀራቸው ድረስ ከመኢሶን ጋር የሚገናኙና የሚደራደሩ ሰዎች ከመሆን አልፈው አቶ መለስ ዜናዊ በአንድ ውይይት ላይ በኢትዮጵያ ምድር ካሉ ድርጅቶች አብረን ልንሰራ የምንችለው ከመኢሶን ጋር ነው ማለታቸው ተመዝግቦላቸዋል:: ዛሬ በዚህ

አባባል እንፈርበት፣ እንኩራራበት ሌላ ጥያቄ ነው። አቶ አበራ የማነአብን የብኤመሪ አንድ የመኢሶን ልዑካን ቡድን «በትግሉ ዘመን» እዛው ትግራይ ድረስ ሄዶ ከህወሃት አመራር ጋር ተወያይቶ ተመልሷል። ታዲያ ይኸንን ሁሉ ጊዜ ከዚሁ ወንጀለኛ ድርጅት ጋር እንዴት እንደዚያ ተዋሩ? እነሱ አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ መኢሶን አይንህን ላፈር የተባለበት ምክንያት በፖለቲካ ልዩነት ሳይሆን በቀይ ሽብር ምክንያት ነው ቢሉ ማን ያምናቸዋል? ሦስተኛ ልዩነቱ ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተራ አሉባልታና ውንጀላ አልፎ በመኢሶን ላይ የሚሰነዘረው ከስ ወደመገናኛ ብዙሃን ተላልፎ አል። በጉባኤው መጨረሻ ላይ የእርቅና ሰላሙ ጉባኤ ዋና አስተባባሪ የቀይ ሽብሩ ተዋናይ ነገደ ጎበዜ መሆኑ ተደረሰበት የሚል መግለጫ አንብቤያለሁ።

በዚህ በሽብር ጉዳይ ለአመጽና ለግድያ በሺህ የሚቆጠሩ ጓደኞቻችንን እንዳላሰዋን፣ ከኢትዮጵያ ገበሬዎች ጐን ተሰልፈን ስንት ለጋ ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን ለባለመሬቶች ጥይት እንዳልዳረግን፣ በ1970 ዓ.ም በመላ ኢትዮጵያ በየከተማውና በየመንደሩ ከአስራ ሰባት ሺህ በላይ መሪዎቻችን፣ አባሎቻችን፣ደጋፊዎቻችንና ከኛ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው ዜጎች በኛ ስም በደርግ እስር ቤቶች እንዳልታጐሩብን፣ በአዲስ አበባ ብቻ በየሳምንቱ ስንትና ስንት ታጋዮቻችን በየመንገዱ እንዳልተደፉብን፣ መሪዎቻችን ከየእስር ቤቱ እየተጎተቱ እንዳልተረሸኑብን፣ በዚሁ በ1970 ዓ.ም ስንት የመኢሶን አባላት የሆኑ የቀበሌ ተመራጮች በግድያ አንሳተፍም በማለታቸው ብቻ በሰበብ አስባብ በሰደድ መሪዎች እንዳልተረሸኑብን፣ በጥቅምት፣ ኅዳርና ታህሣሥ ወራት ወላጆች ልጆቻቸውን ለማትረፍ በአንዳንድ ገና በኛ ቁጥጥር ሥር ለቀሩ ቀበሌዎች ልጆቻችንን ጠብቁልን እያሉ እያመጡ እንዳላስረከቡን፣ አንዳንድ የታሪክ ደንቆሮዎችና የተጨባጭ ሃቅ እውራን እኛን በቀይ ሽብር መወንጀላቸውን ሳይ እንዳንዱ «ይበለን» ለማለት ይቃጣኛል። የመኢሶን ሰዎች፣ በተለይ በአመራር ዙሪያ ያለነው አብዛኞቻችን «ብዕር ገፊ» ከሚባለው ክፍል ሆነን እንዴት ይህንን ጉዳይ ማብራራት አቃተን እያልን መቆጨታችን አልቀረም። ግን ደግሞ ነገሩ ቀላልም ውስብስብም ነው።

ቀላል ነው የምልበት ምክንያት ባለፉት 20 ዓመታት በኢትዮጵያ በተካሄደው የአመጽ ሂደት እንደድርጅት ከሁሉ ባነሰ የተሳተፈ ድርጅት መኢሶን እንደሆነ ለማስቀመጥ የነገሮችን ቅደም ተከተል ማሳየት ብቻ ይበቃል። መኢሶን የዚህ አመጽ ሂደት ተዋናይ ለመሆን ጊዜውም፣ ፍታውም፣ አቅሙም እንዳልነበረው ማሳየቱ ምንም ችግር የለውም።

ግን ደግሞ ጥያቄው ውስብስብ ነው። የፖለቲካና የሞራል ተጠያቂነት፣ የፖለቲካና የሞራል ኃላፊነት የለብንም ወይ? ካለብንስ ምን ያህል ነው የኛ ድርሻ? በጊዜው የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ ሕዝብ ትግል ብለን አስተምረናል፣ ቀስቅሰናል። ሕዝቡ በተቻለ እንዲታጠቅ ሞክረናል። በተለይ የኢትዮጵያ ገበሬዎች ራሳቸውን ከመከላከል አልፈው መሬታቸውንም እጃቸው እንዲያስገቡ ለማድረግ ሞክረናል። የኢትዮጵያችን ባህል አመጽ የተሞላበት ባህል እንደሆነ እንገነዘባለን። የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ታሪክ የአመጽ ታሪክ እንደሆነ እናውቃለን። ዛሬ ይህንን ባህል ለአንዴም ለዘላለምም ለመስበር እንጀምር ብለን የሰላምና እርቅ ጉባዔ እያልን ሳይ ታች እንላለን። ግን ደግሞ እኛም፣ ትውልዳችንም እንዳለ በዚያን ጊዜ ያራመደው የመደቦች ትግል፣ አብዮታዊና ቅዱስ አመጽ፣. . . የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ለዚህ አመጸኛ ህብረተሰብ እንደ እብድ ገላጋይ ዘመናዊ ሽተል ማቀበል ነበር ወይስ ለጊዜው ሁኔታ ተገቢ ምላሽ ነበር? እነዚህ ሁሉ እጅግ ውስብስብ ጥያቄዎች ናቸው። ይህ ወይም ያ ድርጅት ሳይባል ሁሉም ጊዜ፣ ፋታና አመቺ ዲሞክራሲያዊ ሁኔታ ሲገኝ ሊወያይባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች እንጂ መኢሶንንም ሆነ ኢህአፓን ወይም ሌላ ድርጅት በመወንጀል ብቻ የምንሰናበታቸው አይደሉም።

ግን ደግሞ አሁን በመገናኛ ብዙሃን ጭምር መወንጀል ጀምረናልና ቢያንስ በአስተሳሰብ፣ በፖለቲካና በሞራል ኃላፊነት ደረጃ የኛንም፣ የሌሎችንም ድርሻ ለመጭው ሰፊና ትምህርታዊ ውይይት እየተውን ተጨባጩን ሃቅ ለመጠቆም እንገደዳለን።

የኢህአዴግ ውንጀላ መኢሶን በ1969 እና 1970 ዓ.ም የቀይ ሽብር አራማጅ ኃይል ነበር የሚል ነው። እኔንም በዚሁ ወንጀል ከሶኛል። በ1969 ዓ.ም ስለነበረው ሽብርና ስለመኢሶን ሚና ገዞቅ ብየ እመጣበታለሁ። ከወዲሁ ግን 1970 ዓ.ም መኢሶን ቀይ ሽብር አራመደ፣ ሰው ጨረሰ የሚውን በሬ ወለደ ታሪክ ማራገፍ ይቻላል። እኔ አገር ለቅቄ የሄድኩት በሐምሌ ወር 1969 ዓ.ም ነው። በ1970 ዓ.ም በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የተካሄደውን፣ የመኢሶን ጓዶች በገፍ የቀመሱትን አረመኔያዊ ግፍ የተከታተልኩት በውጭ ጋዜጦችና እየተጠናቀሩ ይደርሱኝ በነበሩ የመርዶ ሪፖርቶች አማካኝነት ነበር። በዚህ ጊዜ ፓሪስ ሆኜ አዲስ አበባ ከድርጅቱ አመራር ጋር ግንኙነት ሳደርግ ለግንኙነት የሚሰየሙልን ታጋዮች ተራ በተራ የቀይ ሽብር ሰለባ እየሆኑ በአራት ወር ውስጥ እውጭ ላለነው አገናኝ እየተባሉ አምስት ሰዎች ተፈሪርቀዋል። የሚደርሱት ሪፖርቶች እንዳንዱ በዚህ ሳምንት አዲስ አበባ 20 ጓዶች ተሰውተዋል፣ ጉንደር በዛሬው ዕለት ስድስት ጓዶቻችንን ተረሸኑ፣ ሀረርጌ ይኸንን ያህል ወዛደሮችና የሕዝብ ድርጅት ካድሬዎች የሱማሌ ሠርጉ ገብ ተብለው ተረሽነዋል፣ ዛሬ ዶ/ር ከድር መሀመድና ዶ/ር ዮሃንስ መስፍን ከታሰሩበት ተወስደው ተረሽነዋል፣ በጥቅምት ወር መጨረሻ ላይ አድር ባይ የቀበሌ መሪዎች ስብሰባ አድርገው «ነጻ ርምጃ» ብለው በሰፊ ግድያ ለማስማራት ውሳኔ ተወስዷል፣ ብርሃኑ ገመዳ እጀን ለደርግ አልሰጥም ብሉ ራሱን ሰዋ፣እነ ዶ/ር ተረፈ ወልደጻድቅና ባለቤቱ አጥናፍ ከሌሎች አስራ አንድ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ጋር አምቦ አጠገብ ተይዘው እጅ ከሰጡ በኋላ እዛው የተያዙበት ቦታ ከትላንት ወዲያ ተረሽነዋል፣ ከኢህአፓም ከመኢሶንም፣ ከየትም የሌለበት ወጣት ጭምር በገፍ እየረገፈ ነው. . . የሚል ነበር። በነዚያ አስከፊ ወራት እያገዳገዱን ሪፖርትም ሆነ ቴሌግራም ስከፍት እየሰቀጠጠኝ፣ ሳነብ እንባ እየተናነቀኝ ነበር። ታዲያ ይህንን ሁሉ ሕይወት የኖርኩ ሰው መኢሶን በ1970 ሽብር አራመደ፣ ሰው ጨረሰ ሲባል፣ ለመኢሶን ሳይሆን ይህንን የተገላቢጦሽ ታሪክ ሆን ብለው ለሚያራምዱት፣ እያዩ አውቀው የሃቅ እውራን ለሆኑ ኃይሎች አፍርላቸዋለሁ።

ያኔ ደግሞ ይህ እልቂት እንዲቆም በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለይ በጊዜው የደርግ ወዳጆች በነበሩ ሀገሮች አካባቢ የተቻለኝን እንድገስራ ከመኢሶን አመራር በተላለፈኝ መመሪያ መሠረት የተቻለኝን ተሯሩጫለሁ። በ1970 ዓ.ም እኔ የኢትዮጵያን ምድር የረገጥሁት ቀይ ሽብር ለማራመድ ሳይሆን በሚያዝያ ወር በኩባዎች አማካኝነት ከኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ጋር ለመደራደር ሽብር እንዲቆም ለመሟገት ነበር። የሰው ነፍስ እንደዚያ በረከሰበትና ከጢፍ በማይቆጠርበት ወቅት ነፍሴን ሸጪ አዲስ አበባ ተመልሼ ነበር። በዚያን ጊዜ ኩባ፣ የመን፣ ቡሩት ፍልስጤሞች ጋር ላይ እታች እያልኩ ድርድር የሞከርኩት በመኢሶን አመራር ትእዛዝ ይህ ሽብር የሚቆምበትን ሁኔታ ለመፍጠር ነበር።

የ1970 ዓ.ም ጉዳይ ቀላል ነው ያልኩት ትክክለኛ አእምሮ ላለው ሰው፣

ሐቁን ልመልከት ካለ እንደዚሀ ግልጽ በመሆናቸው ነው። ውስብስብነቱም እንደዚያው ነው። በዚያ አሳዛኝና አስከፊ ሁኔታ ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ ወጥተው እንደነበረና ሀገሪቱ አስቸጋሪ የአመጽ አዙሪት ውስጥ ገብታ እንደነበረ ግልጽ ነው። ይህ ሁኔታ እንዲፈጠር ያገዙትና አስተዋጽኦ ያደረጉት የመኢሶን የፖለቲካ፣ የአስተሳሰብ፣ የድርጅታዊ አሠራር ስህተቶች ምንድን ናቸው? የኢህአፓስ? የህወሃትስ? በጠቅላላው የዚያ ታጋይ ትውልድ ምን ምን ስሁተቶች ናቸው ያንኑ ትውልድ እንደዚህ ለመከራ የዳረጉት? እነዚህ ሁሉ ረዥምና ትምህርታዊ ውይይት የሚጠይቁ ጉዳዮች እንጂ ነገሮችን በዚህ ወይም በዚያ ድርጅት ላይ በመለጠፍና የፖለቲካ ንግድ በማካሄድ የምንገላገላቸውና የምንስነባበታቸው ጥያቄዎች አይደሉም።

መኢሶን በበኩሉ ያቅሙን ትምህርት ቀስሟል። ፋታ ወስዶ የመወያየት ያህል ነገሮችን ከቁጥጥር ውጭ እንዳይወጡ የሚያስችል መፍትሄ የለም የሚል ቀላል ትምህርት ቀስሟል። ከዚህ ቀደም እንደገለጽሁት ከቅንጅቱ አመራር ጋር እነ አበራ የማነአብ የሰላምና እርቅ ጉባዔ አያሱ የታገሱትና ከፓሪስ እስከ አዲስ አበባ ያደረገነው ጉዞ የኛም የኢህአፓም ታጋዮች ካለፈው ትግላችን ያገኘነው ግንዛቤ ውጤት ነው።

እንግዲህ መኢሶን በቀይ ሽብር ከሚከሰስባቸው ሁለት ዓመታት አንዱን ከነመከራው፣ ከነግፉ፣ ከነእንገባው፣ ገና ለሀገርና ላሕዝብ ደህንነት ሲባል ከሚጠይቀው ትምህርታዊ ብሔራዊ ውይይት ጋር ለጊዜው እዚሁ ላይ ልንተወው እንችላለን። በደፈናው ሳይሆን በዚህ ወቅት መኢሶን በዚህ በዚህ ተጨባጭ ወንጀል ይከሰሳል የሚሉ ከሆነ ሦስት ዓመት ሙሉ የደርግንም የመኢሶንንም ፋይል በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው ሲመረምሩ የቆዩት ኢህአደጎች እስቲ ያገኙትን መረጃ ያውጡ።

የ1969 ዓመትም ቢሆን ከነተጨባጭ ቀናቱ፣ ከነተጨባጭ ሃቆቹ፣ ከነውስብስብ የፖለቲካ ሂደቱ የሚመረመር እንጂ እንደዚሁ «መኢሶን ቀይ ሽብር አራመደ» በሚል አሉባልታ የምንሰናበተው አይደለም። ያ ዓመት እጅግ ውስብስብና በተከታዮቹ ዓመታት ለኢትዮጵያ የወደፊት እድል ወሳኝ የሆነ ዓመት ነበር። በገጠር ቀደም ሲል ተፈጥሮ የነበረው የዘማቾችና የአርሶ አደሩ ህብረት አሁን ደግሞ ከአባላቱ 70 ከመቶ በላይ የቀድሞ ዘማቾችን ባሰማራው የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ታጋዮችና በገበሬው ህብረት ተተክቶ አብዮቱ ከሚጠይቀው መስዋዕትነት፣ ከሚያስከትለው ውጣ ውረድ ጋር ወደፊት እየገሰገሰ ነበር። ገበሬዎች መሬታቸውንም ነጻነታቸውንም ያው ዘማቾችን ሲያስቸግሩ ከነበሩት ከደርግና ከቢሮክራሲው አባላት፣ ከየክፍለ ሀገሩ ፖሊስ፣ ከአጥቢያ ዳኞችና ምስለኔዎች፣ ከታጠቀ ባለመሬት ጋር እየተናነቁ የነበሩበት ወቅት ነበር።

በከተማ ያለው ሁኔታ ይበልጥ አስቸጋሪና ውስብስብ ነበር። ኰሎኔል መንግሥቱ መኢሶንን ከቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ያደረጉት ሙከራ ሁሉ አልሳካ ብሏቸው የራሳቸውን ድርጅት «ሰደድ» ብለው በግንቦት ወር 1968 አቋቋሙ። በዚያ ወቅት እነመቶ አለቃ ዓለማየሁና ሻምበል ሞገስ ሰደድን አብረው ከመሰረቱ በኋላ ከኰሎኔሉ ጋር ቅራኔ ውስጥ ገብተው መቶ አለቃ ዓለማየሁ የኰሎኔሉ «ደንቆሮ አሽከሮች» በሚሏቸው እየተተኩ ድርጅቱን ለቀው ሄደዋል። ኰለኔሉንና ሰደድን ለመዋጋት ድርጅታዊ መሠረት ለማግኘት ከኢህአፓ ጋር ተቀራርበዋል። በኋላ እንደሰማሁት በዚሁ በ1968 ዓ.ም በነሐሴ ወር ዓለማየሁ የኢህአፓ አባል ሆኖ ነበር ይባላል። ኰሎኔል ይኸን ሲጠረጥሩ እነዓለማየሁን ህገ ወጥ ለማድረግ ኢህአፓን በመንግሥት ደረጃ ለማውገዝ ይነሳሉ። ከኢህአፓ ገጥሟል ብለው የገመቱትን ሁሉ ጸረ መንግሥት ብለው በመወንጀልና በማስወንጀል ለመምታት እንዲያመቻቸው ነው። በዚህን ጊዜ እኛ እዛው እስራቸው ቁጭ ብለን ሰዎቹ ትንሽ ተቀያይመዋል ከማለት አልፈን የሞት ሽረት ትግል ውስጥ እንደገቡ ልብ አላልንም። በኋላ ነው የሚገባን።

እንግዲህ የነሱ የሞት ሽረት ትግል በዚህ አኳኋን ውስጥ ውስጡን ተጀምሯል። እኛስ? መኢሶን በገጠር በአጠቃላይ መተከሉና በየጊው በየቦታው በሚፈጠሩት ግጭቶች ልክ እንደዘማቾች የገበሬው ወገን እየሆነ «አስቸግሯል» በማለት ቢሮክራሲው ይጠላዋል። ኰሎኔሉ ነጻ ድርጅት መሆኑን አልወደዱትም። ግን ደግሞ ገጠሩን እየያዘ ነውና ምናልባት አንድ ቀን አዲስ አበባ በኩዴታ ብገለበጥ የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ያስፈልገኛል ብለው ያምናሉ። ይህንን ጉዳይ ከኔ ከራሴ ጋር ብዙ ተወያይተዋል። «ችግር ቢፈጠር አዲስ አበባ የእናንተ ታጋዮች ገበሬውን የያዙትን ያህል ተዋግተው ሊያዋጉ የሚችሉ ናቸው ወይ? ይህ ነበር የጥያቄዎቻቸው ተደጋጋሚ ይዘት፣ ደርግ ቡና ቤት አብረን ስናመሽ፤ ይህ ደግሞ ትክክለኛና ከኃላፊነት የመነጨ ውይይት ነበር። አዲስ አበባ ሁኔታው ጨርሶ አያስኦማምንም። የኛ የመኢሶናች ኃይል ደግሞ በርግጥም ገጠር ነበር።

መኢሶን ከኰሎኔሉ ነጻ የሆነ ድርጅት ቢሆንም እነዓለማየሁ እሳቸውን መልምለን የጨረስን አድርገው ገምተዋል። እርግጠኞም ነበሩ። ስለሆነም ቀስ በቀስ ከኰሎኔሉ ጋር ያላቸው ትግል ከኛም ጋር እየመሰላቸው እነሱ ደግሞ በበኩላቸው ኢህአፓን የመያዙን ጥረት ገፉበት። በዚህ ላይ ዶ/ር ሰናይ ልኬና «ወገዘ» አሉ። ዶክተር ሠናይ ቀደም ሲል ጀምሮ «ወደ ሶሻሊዝም በወታደራዊ ጉዳና» ብሉ የሚያምን ሰው ነበር። ሠራዊቱም ውስጥ በግልጽና በገፍ ይመለምል ነበር። እሱም የመኢሶን ነገር አስገቶታል። ያኔ በተለይ ወጣቱ የሚያውቀው «ሁለት መስመር» ብቻ ነው። ወገዘ እምብዛም አይታወቅም ነበር። በተለይ ደግሞ ከ1968 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ በጋዜጦች የተካሄደው ክርክር ለመኢሶን እጅግ እንደጠቀመ ይታያል። ከኢህአፓ ወገን በሌላው መስመር እየተማረከ የሚፈልሰው ወጣት በአዲስ ዘመን ላይ ያን ክርክር ሲያነብ ማን ጻፈው? አይልም። የመኢሶን ይመስለዋል፣ ሁሉም። ስለዚህ ከኢህአፓ ሲፈልስ የሚመጣው ወደ መኢሶን እንጂ ወደ ወገዝም ወደሰደድም አልነበረም። «መኢሶን በገጠር አየለ፣ በከተማ አበጠ» ተባለ። ሰደድም ወገዝም የመኢሶንን እድገት ለመግታት ሞከሩ። ሰደዶች ምንም ቢሆን አንድ የምሁር ክንፍ ስለሚያስፈልጋቸው፣ ወዞች ደግሞ የወታደርም ሆነ የቢሮክራሲ ጡንቻ ያስፈልገናል ብለው ስላመኑ ከሞላ ጎደል በነሐሴ ወር 1969 አካባቢ ወደሰደድ እንዲደባለቁ ስምምነት ተደረሰ። ድርብ አባልነት እንደያዙ። እነፍቅረስላሴ ድርብ አባላት ነበሩ። በኋላ ድሮውንም በስምምነት የወዝም የሰደድም የሆኑት መኰንኖች ከነለገሠ ጋር ሲጣሉ «የወገዘ ሰርጉገቦች» ተብለው እየተለቀሙ ተረሸኑ። ይኸ ግን ቆይቶ ነው።

እንግዲህ 1969 ዓ.ም መግቢያ ላይ መኢሶን በገጠር «ውሃ ውስጥ እንዳለ ዓሣ» ቢሆንም በከተሞች በተለይ በአዲስ አበባ ወዝና ሰደድ እድገቱን በሆነው መንገድ ለመግታት የተነሱበት፣ ኰሎኔሉ ለጊዜው ከነአለማየሁና ከኢህአፓ ጋር ለገጠሙት ትግል፣ ለወደፊቱ ደግሞ ምናልባት አንድ ቀን ሊመጣ ለሚችል የገጠር ትግል ሲሉ የታገሱት ቢሆንም የማይዋጥ የማይተፋ ጉድ ሆነባቸው። ለነገሩ ግን እነዓለማየሁን ለማስደንገጥ የመኢሶን ምልምል እስከመምሰል የሚሄዱበት ወቅት ነበር። ይኸ ሁሉ ዛሬ ከነገሮች ራቅ ብዬ ሳስበውና ስተነትነው የሚታይ፣ ጥርት ያለ ነገር እንጂ ያኔማ በየትኛው ፋታ ነገሮችን ማሰላሰል ይቻል ነበር?

የኢህአፓን በአዋጅ በደርግ መጠንገዙና ህገወጥ መሆን ምክንያት ምን እንደሆነ ወደፊት በሰፊው የሚያወቁ ሁሉ ይጽፉታል። ገን እዚህ ላይ በኋላ ለተከተለው ችግር ትልቅ ሚና ያለው ስለሆነና በዚያ የተወሳሰቡ ቅራኔዎች ክልል ዒላማ የነበረው ኢህአፓ ብቻ ሳይሆን መኢሶንም እንደነበረ ለማሳየት ትንሽ ማለት ያስፈልጋል። ኢህአዴጎች የዚህን ውይይት ፋይልና በዚያን ጊዜ የእኛ አቋም ምን እንደሆነ የጊዜውን ታሪ ጉባኤ በመረምሩ ያገኙታል።

ነሐሴ 1968 አጋማሽ ላይ ነው። ኩሎኔል መንግሥቱ አንድ ቀን በሮዬ ደውለው «አሥራ አንድ ሰዓት ላይ ብቅ በል ጥብቅ ጉዳይ አለኝ» አሉኝ። በተጠሮ ሰዓት ስሄድ እንዲሁ እንደኔው የተጋበዙ ከኛ አባላት ፍቅሬ መርዕድንና ተስፋየ ታደሰን አገኘሁ። ሁላችንም ለምስጢርና ጥብቅ ስብሰባ ተጠርተን ነው የመጣነው። ስብሰባው ላይ ሰናይ ልኬ! መቶ አለቃ ግርማ ነዋይ! ኩሎኔል ተስፋዬ ወልደሥላሴ ነበሩ። ኩሎኔሉ ኢህአፓን እየወረፉ ውርጅብኝ ሲደረድሩ ነገሩ አልገባኝም። ቀስ ብለው ወደ ፍሬ ነገሩ ሲገቡ «ዛሬ እዚህ የሰበሰብኳችሁ በኢህአፓ ላይ በመንግሥት ደረጃ የማጋለጥ ዘመቻ ስለምንጀምርበት ሁኔታ እንድንወያይ ነው» አሉ። እኔም ፍቅሬም ተስፋየም ቀደም ብለን ባንመካከርም እንደ አንድ ሰው ተቃወምናቸው። «መንግሥት እዚህ ውስጥ አይገባበት። ውይይት በጋዜጣ እየተካሄደ ነው! ኢህአፓን ቀስ በቀስ በውይይት መርታት ይቻላል! ቀስ በቀስ ወጣቱን ከሱ ማላቀቅ ይቻላል። መንግሥት ከገባበት ለኢህአፓ ይበልጥ ዝናና በተለይ በወጣቱ ዘንድ ይበልጥ ተቀባይነት ለማስገኘት ይረዳዋል።» የሚል መከራከሪያ ስናቀርብ ስለመንግሥትና የመደቦች ትግል ሰፊ ገለጣ ተደረገልን። በተለይ በሰናይና በግርማ። አስበንበት እንምጣ ብለን ተለያየን።

ወዲያው ወጥቼ ከበደ መንገሻ ዘንድ ሄጀ የሆነውን ሪፖርት አረግሁ። እብድ ነው የሆነው። መጀመሪያ ያለኝ «ሰማ ነገደ! ይሄ ጸረ ኢህአፓ ርምጃ አይደለም። ጸረ መኢሶን ሴራ ነው። በጋዜጦች ውይይት እነሰናይ ምንም ጥቅም ስላላገኙና በነሱ ሳቢያ መኢሶን በወጣቱ ዘንድ እያየለ ስለመጣ ይህንን ሂደት ለማደናቀፍ ነው። ለመሆኑ ኢህአፓን እንደዚህ በመንግሥት ደረጃ እናውግዘ! ሕገወጥ እናድርግ ሲሉ በሚከተለው የግድያ ዘመቻ ወጣቱ ምን ሊሆን ነው? ትጥቅ ይሰጡታል? ይህንን እብደት መቃወም አለባችሁ» የሚል መመሪያ ነው የሰጠኝ። እንደገና ተሰበሰብን። ብዙ ተጨቃጨቅን። ኩሎኔሉ በድምፅ ብልጫ አሉና ተሸነፍን። ይህንን ውሳኔ እንደምቃወም ይመዝገብልኝ አልኩ። ተስፋየ ታደሰም እንደዚሁ አስመዘገበ። ከወር ተኩል በኋላ የግድያ ሰለባ ከሆኑት ከመጀመሪያዎቹ አንዱ ፍቅሬ መርዕድ ከመብሸቁ የተነሳ እንደኛ ይመዝገብልኝ እንኳ አላለም።

እዚህ ላይ መግባባት ያስፈልጋል። ኢህአፓና መስመሩ ለምን ተወገዘ አይደለም ክርክሩ። «መንግሥት አይግባበት! ጉዳቱ ያመዝናል» የሚል ነው። «አደገኛ ነው። ሰበብ መስጠት ነው።» የሚል ነበር ክርክራችን።

እንደተፈራው እነገለማየሁ የዚህ ሴራ ዒላማ መሆናቸው ግልጽ ስለነበረ አበዱ። መጀመሪያ እኛ ላይ። ወደዚህ ርምጃ ኩሎኔሉን የመራነው እኛ መስለናቸዋል። በዚያን ጊዜ ከገለማየሁ ጋር እንቀራረብ ስለነበረ ከበደ የሆነውን ሁሉ እንዳስረዳ! ደግሞም ከኢህአፓዎች ጋር ግንኙነት እንደጀመረ ያጫወተኝ ስለነበረ ለነሱም መልእክት እንዳስተላልፍ በሱ በኩል ተላኩኝ። ገና ስገናኝ ወረደብኝ። «በኛው ገንዘብ እንደዚህ አበጣችሁ! አሁን ደግሞ በመሃከላችን ገብታችሁ ታበጣብጡን ጀመር! የኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋረዳችኋል! ወዘተ።»

ነገሩን ለማብረድና በጥሞና ለመወያየት የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር የአኩል ሰዓት እድሜም አልወሰደ። ለኛ የለንበትም ማለት ብቻ አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ ርምጃ ለምን! ከፖለቲካ አንጻር ለእኛ እንደማይጠቅመን! ለምንስ ይህንን ጉዳይ ለኢህአፓ አመራር ማስተላለፍ እንዳለበት! ለምንስ እነሱ እንዲህ ዓይነቱ ተንኰሣ ውስጥ መውደቅ እንደሌለባቸው . . . መልእክት እንዲያስተላልፍ ጠየቅሁት ተስማማ። ከበደ በሰጠኝ ተልእኮ መሠረት አስፈላጊ ከመሰላቸው ተገናኝተን ልንወያይ ፈቃደኛ መሆናችንን እንዲነግራቸው ጠየቅሁት። ገለማየሁ እሺ እንዳለው! መልእክቱን ያስተላልፍ፣ አያስተላልፍ፣ አላውቅም። የሆነ ሆኖ አገሪቱን ከብዙ ጥፋት ሊያድን የሚችል የውይይት አጋጣሚ አመለጠን። ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ ብዙ እንደዚህ ዐይነት እድሎች እንዳመለጡን ሳስብ አንዳንዴ ለራሴ «ይቺ አገር ያመለጡ የታሪክ አጋጣሚዎች አገር ሆና እስከመቼ?» እያልኩ እጠይቃለሁ። እነ ኢህአዴግ የፖለቲካ ስልጣን ሽሚያ ይመስላቸዋል ወይም ደግሞ ስለዚች አገር የወደፊት እድል ደንታ ቢስ ሆነው ነው እንጂ አሁንም እንወያይ! ይህ የሽግግር ዘመን የሚሰጠን የታሪክ አጋጣሚ እንዳያመልጠን ስንል ከዚህም ከፉ ልምድ ተነስተን እንደሆነ የገባቸው አይመስለኝም።

የሆነ ሆኖ 1969 ዓ.ም በዚህ የፖለቲካ አካባቢ ተጀመረ። ሽብርን በሚመለከት እኔ ሦስት የተለያዩ ወቅቶችና የተለዋወጡ የፖለቲካ ኃይል ሚዛኖች ይታዩኛል።

የመጀመሪያው ወቅት ከመስከረም አጋማሽ እስከ ኩሎኔል መንግሥቱ መፈንቅለ መንግሥት ማለትም እስከ ጥር መጨረሻ ድረስ ያለው ወቅት ነው። ይህ ወቅት ራሱ የፖለቲካ ኃይል ሚዛን ተቀያይሮበታል። እስከ ታህሣሥ 1969 ዓ.ም ድረስ በነመንግሥቱ ቡድንና በነገለማየሁ ቡድን ጨርሶ ያልለየለት የፖለቲካ ትግል! ከዚያ በኋላ የደርግን መዋቅር በማሻሻል ስም የኩሎኔል መንግሥቱ መሸነፍና የነገለማየሁ የማየል ወቅት። ይህ ወቅት ነበር። ለመኢሶንና ለቀበሌ ተመራጮች ምንም ለውጥ አልነበረውም። እነዚህ አምስት ወራት ራሳቸውን ለመከላከል ምንም መሣሪያ ስላልነበራቸው! እነ ገለማየሁ በደርግ ውስጥ እያየሉ በሄዱ ቁጥር ይበልጥ እየተጠቁ የሄዱበት ወቅት ነው። መኢሶን በዚህን ወቅት ምንም የታጠቀ ኃይል አልነበረውም። ቀበሌዎችም በነገለማየሁ አሻፈረኝ ባይነት ትጥቅ ተነፍገቻው! የመዘደር መሪዎችም እንዲሁ ባዶ እጃቸውን የሚጠቁበት ወቅት ነበር።

በዚህ ወቅት በኢህአፓ አመራር የመጀመሪያው የግድያ ሙከራ የተደረገው መስከረም 13 ቀን ሐሙስ በኩሎኔል መንግሥቱ ላይ ነበር። ይህ ሳይሳካ ከቀረ በኋላ ነው የግድያው ዘመቻ በተለይ በወጣቶች፣በቀበሌ ተመራጮችና በሕዝብ ድርጅት ካድሬዎች ላይ ማተኩር የጀመረው። የመጀመሪያው ግድያ እሁድ መስከረም 16 ቀን አንድ የመኢሶን ወጣቶች የጥናት ቡድን ስብሰባ ላይ እንዳለ በድንገት የኢህአፓ ወጣቶች ደርሰው በውይይት ላይ ባሉት ስድስት ልጆች ላይ ተኩስ ሲከፍቱ ከስድስቱ ልጆች ሦስቱ ወዲያው ሲሞቱ የተካሄደ

ነው። ከዚህ በኋላ መስከረም 21 ቀን ፍቅሬ መርእድ ይገደላል። ከዚያ ምንም ማቆሚያ አልነበረውም። በአዲስ አበባም በክፍለ --- ሀገር ከተሞችም፣ በየትምህርት ቤቶችም፣ በየቀበሌው፣ በየፋብሪካው፣ በየመንገዱ ያልታጠቁ ታጋዮች መርገፍ ይጀምራሉ። ይህንን ግድያ አስመልክቶ የኢህአፓ አመራር ያወጣው ዲሞክራሲያ እስካሁን ይገርመኛል። በሦስተኛው ዓለም አገሮች አብዮት ማራመድ የሚቻለው በገጠር የትጥቅ ትግል ቢሆንም በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የከተማ የትጥቅ ትግል አስፈላጊ መሆኑን ብቻ ሳይሆን የሚቻል ነው ብለን ጀምረነዋል የሚል መግለጫ ነው። ግን የጦሩ ትግል ምኑ ላይ እንደሆነ እስካሁን አይገባኝም። ከደርግ አባላት፣ ከታጠቀው ሠራዊትና ፖሊስ ጋር ሳይሆን ግድያው የሚካሄደው ባልታጠቁ ታጋዮች ላይ ነበርና። መኢሶን አባላቱንና ደጋፊዎቹን ለመጠበቅ እስከ ጥር መጨረሻ ድረስ ምንም አጸፋ ርምጃ አልወሰደም። ለምን?

ዋናውና የመጀመሪያው ምክንያት በተለይ ያ ሁላችንም እንደ ታላቅ ወንድማችንና ብዙ ሰጋ ታጋዮቻችን «ጋሼ» እያሉ የሚጠሩት መሪያችን ዶክተር ከበደ መንገሻ በዚህ ጉዳይ የወሰደው የፖለቲካ አቋም ነበር። ሁለት አስተያየቶች ነበሩ። በአንድ በኩል ስሜታዊ የሆነና (እኔም ራሴም ይኸርው የነበረ) «ሰዎቹን እናውቃቸዋለን። ለምንድን ነው እኛስ የ20 የ30 ሰው ኮማንዶ አቋቁመን ራሳችንን የማንከላከለው? ታጋይ ቢሞት ትግል አይሞትም እያልን እስከመቼ?» የሚለው አቋም ሲሆን «ትግሉ እስከዚህ ድረስ በኢህአፓ መሀከል አይደለም። ኢህአፓዎች ርግጥ የራሳቸው ዓላማ ይኖራቸዋል። ግን በዚህ የግድያ ሂደት ከጀርባቸው ሆና እንዳንዱ፣ እንዲያውም በነሱ ስም በራሱ ኃይል የሚንቀሳቀስና በግድያ የተሰማራ የፖሊሱ፣ የሕዝብ ደህንነቱ፣ የቢሮክራሲው ስውር ኃይል አለ። በዛሬው ወቅት ይህንን የማይናቅ ስውር ኃይል አስተባብሮ አመራር መስጠት የሚፈልግና የቻለ በየዕለቱ በደርግ ውስጥ እየተጠናከረ የመጣ የነዓለማየሁ/ሞገስ ክሊክ አለ። በገጠር ከገበሬው ጐን ቆመን ይህንን ግንባር ድል አርገነዋል። በከተማ ብቻችንን እንግጠመው፣ እዚህም እዚያም አንዳንድ ኮማንዶዎች አቋቁመን የኢህአፓን መሪዎች በማደን እንሰማራ ማለት «ስዊሳይዳል» ነው። አንደኛ ነገር አንችላቸውም። ሁለተኛ ነገር ዋናውን ባለጉዳይ የከተማውን ሕዝብ ተመልካች ብቻ ማድረግ ነው። ስለሆነም የኛ ዋናው ትግል በሁለት የተያያዙ ጥያቄዎች ዙሪያ ማለትም በዲሞክራሲና በትጥቅ ጥያቄ መሆን አለበት እንጂ በግለሰብ ግድያ መሰማራት ትልቅ ስህተት ነው» የሚል ክርክር ነበር። ለዚህ ነው በዚያን ጊዜ ባለን በሌለን ኃይል የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች በየፋብሪካውና በየቀበሌው እንዲቋቋሙና እንዲታጠቁ የታገልነው።

ሁለተኛው ምክንያት በዚያን ጊዜ እንኳን ይህንን ከባድ ስውር ኃይል ቀርቶ ኢህአፓ ብቻውንም ቢገጥመን እሱን የምንቋቋምበት አቅሙም አልነበረንም። መሣሪያ የለንም። ከስንት ጭቅጭቅ በኋላ ከሐምሌ/ነሐሴ 1968 ጀምሮ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ዋና ዋና መሪዎች ለራሳችን መከላከያ መሣሪያ ተሰጥቶናል። ጥቅምትና ኅዳር ላይ በጣም ለተጋለጡ አንዳንድ የሕዝብ ድርጅት ካድሬዎች ፊሉሸር መሳይ ሽጉጥ ተሰጥቷል። ሌላው በየቀበሌው፣ በየፋብሪካው፣ በየት/ቤቱ ያለው ታጋይ ባዶ እጁን ነው። የዚያን ጊዜ ትዝ ይለኛል፣ ባይሆን ኢህአፓዎችን በፕሮፓጋንዳ እናስደንግጥ ተብሎ በሌላ ነገር ገዝም ብለን «ባንዳዎች ከእግር እስከራሳቸው እየታጠቁ ነው» ብለን ወሬው በሰፊው እንዲናፈስ ስናደርግ።

የሆነ ሆኖ የዚያን ጊዜ በተደጋጋሚ የአዲስ አበባ ህዝብ በመቶ ሺህ እየተቆጠረ ሰልፍ ሲወጣ ይይዛቸው የነበሩት መፈክሮች የዚህ ችግርና የዚህ የመኢሶን የፖለቲካ አቋም ነጸብራቆች ነበሩ። «አስታጥቁን አስታስጨርሱን፣ ልምጫችን አስጠቃችን!» ወደኋላ ላይ ደግሞ ቢቸግረን «ወይ አስታጥቁን፣ ወይ ትጥቅ አስፈቷቸው» ወደሚለው ጥያቄ ዞረን ነበር። «አብዮታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ይሸጋገር» የሚለውም የጊዜው የሰልፎች መፈክር የዚህ የተከላካይነታችን ውጤት ነበር።

በዚያን ጊዜ የነበረው የፖለቲካ ሁኔታና በተለይ በደርግ ውስጥ በአንድ በኩል በኰለኔል መንግሥቱ በሌላ በኩል ደግሞ በነዓለማየሁና ሞገስ ቡድን ይካሄድ የነበረው ፍልሚያ ይህንን የግድያ ሂደት የሚያግዝ እንጂ የሚያበርድ አልነበረም። የኢህአፓ አመራር በዚህ ዘመቻው የፈለገውን ዓላማ ሊይዝ ይችላል። ግን እኛ በዚያን ጊዜ የታየን እነዓለማየሁ የሚያንቀሳቅሱት ስውር ኃይል በግድያው መቀጠል የፖለቲካ ጥቅም ነበረው። በመሆኑም በአንድ በኩል የመኢሶን ታጋዮችም ሆኑ ቀበሌዎች የሚጠይቁትን ትጥቅ እንዳያገኙ እያከላከለ በኢህአፓ አመራርም ሆነ በእሱ ስም የሚካሄደው የግድያ ዘመቻ እንዲቀጥልና እንዲፋፋም ይሠራ ነበር።

ከላይ እንዳልኩት እነዓለማየሁ ሰደድን ለቀው ከወጡ በኋላ ኰለኔሉ መኢሶንን ከያዙ ~~እና ደግሞ ኢህአፓን~~ እንጠጋ ብለው ወስነዋል። ኰለኔሉ ተሽቀዳድመው ኢህአፓን ህገወጥ ድርጅት አደረጉባቸው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የነሱ ጸረ መንግሥቱ ትግል የሚንጸባረቀው የያዙት ከሚመስላቸው ከኢህአፓ ጋር ደርግ ተደራድሮ እነሱ የዚህ ኃይል መሪዎች ሆነው ኰለኔሉን፣ ሰደድን፣ መኢሶንንና ይኸው ድርጅት የሚመራቸውን ቀበሌዎችንና የወዛደር የሞያ ማኅበራትን በሌላ ሰፊ መሠረት ባለው ኃይል ለመቋቋም ነበር። ለዚህ ደግሞ ኢህአፓ ታላቅ ድርጅት ነው። ያም ሆና በሁለት የምሁራን ቡድኖች የስልጣን ሽሚያ ትግል ሀገሪቱን ወደአላስፈላጊ ትርምስ መጨመሪያቸውን ለማጠናከር እንደነበረ ያኔም ለኛ ግልጽ ነበር።

የኢህአፓ አመራር እነ ዓለማየሁን ወደራሱ ያድርግ እነሱ ይቅረቡት በእውነቱ መናገር ያስቸግረኛል። በጊዜው የምናውቃቸው የኢህአፓ መሪዎች እነዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ፣ እነክፍሉ ታደሰ፣ እነብርሃነ መስቀል ረዳ በተዘዋዋሪ በዓለማየሁ በኩል ልናስተላልፍላቸው እንሞከረው የነበረው መልእክት ይድረሳቸው አይድረሳቸው በርግጥ ለመናገር አልችልም። ምናልባት ክፍሉ ታደሰ በህይወት አለና እሱ ይኸንን ምስጢር ሊያብራራልን ይችላል። ግን አንድ መናገር የምችለው ነገር ቢኖር ዓለማየሁ በራሱ እምነትና ስሌት ይሁን በሌሎች ጸረ መኢሶን ኃይሎች ግፊት እኛን ጨርሶ የማጥፋት አዝማሚያ ማሳየት እስከጀመረበት እስከ ጥር ወር 1969 አጋማሽ ድረስ ከበደ ገፋበት እያለኝ ተከታታይ ግንኙነት ነበረኝ። በይፋ በደርግ ቡና ቤትና በኔም በሱም ቢሮ። ብዙውን ጊዜ ግን በሱ መኪና ከአዲስ አበባ በኰተቤም፣ በገፈርሳም በኩል ወጣ እያልን እንወያይ ነበር።

በእነዚህ ውይይቶች እሱ ደጋግሞ የሚለው «ከኢህአፓ ግራ ክንፍ ጋር ግንኙነት አለኝ። ከነሱ ጋር እኛም እናንተም መሥራት እንችላለን። ኢሕአፓዎች አንድ ግለሰብ/ ማለትም ኰለኔሉን/ ስለተቃወሙ ዓይናችሁን ላፈር መባል የለባቸውም።» የሚል አነጋገር ነበር። በኛ በኩል ደግሞ ኢህአፓን በማግለል ምንም ጥቅም የለንም። ሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ሲቋቋም እነሱም እንዲገቡበት እንጂ ብቻችንን ለመያዝ ምንም እቅድ እንዳልነበረን፣ አሁንም በኛ በኩል ከነሱ ጋር ለመደራደር ምንም ችግር እንደሌለብን፣ ግን በቅድሚያ የግድያ ዘመቻቸውን ማቆም እንዳለባቸው፣ ይህም አቋማችን ለአመራሩ እንዲነገር የኛ አመራር

ፈቃደኛ እንደሆነ አብራራለት ነበር። ልድገመውና ይህ አቋማችን ለኢህአፓ አመራር ደርሶት በገተት ችላ ይበለው ወይስ ግለማየሁ ሆነ ብሎ ለነሱ ከማስተላለፍ ይቆጠብ አላውቅም።

የነበረ አቋም እንደሆነ ግን ለመጠቆም አንዳች አጋጣሚ መጥቀስ እችላለሁ። የደርግ አባላት ሁሉ ያውቁታልና። በኀዳር/ታህሣሥ ወር እነ ግለማየሁ የደርግን መዋቅርና ፖሊሲ በማሻሻል ስም የኩሎኔል መንግሥቱን ስልጣን ለመቀነስ በጣም ይታገሉ ነበር። ከፍ ብየ እንዳልኩት በደርግ ስብሰባዎች እየደጋገሙ የሚያነሱት ነጥብ ከኢህአፓም ጋር አብረን እንስራ የሚል ኩሎኔል መንግሥቱና ደጋፊዎቻቸው የሚቃወሙት ነጥብ ነበር። በአንዱ ስብሰባ ላይ ኩሎኔል መንግሥቱን «ይህንን በጋራ የመሥራት አቋም የምትቃወመው አንተ ብቻ እኮ ነህ። እነነገደ ጋር ተነጋግረን እነሱ እንኳን ከኢህአፓ ጋር አብረን መሥራት እንችላለን ብለዋል» ብሎ እንደተናገረ አውቃለሁ። ወዲያው ከስብሰባ እንደወጡ ኩሎኔል መንግሥቱ ኃይሌን ቢሮአቸው ጠርተው «ነገደ ከነግለማየሁ ጋር ይሠራል ወይ? መጠቀሚያ እያደረገው ነው። ዛሬ በስብሰባ ላይ በእናንተም ተጠቅሞ ሊከራከረን ሞክሯል» ብለውታል።

የሆነው ሆኖ በታህሳስ ወር ኩሎኔል መንግሥቱ በደርግ ውስጥ በድምጽ ብልጫ ተሸንፈው እነግለማየሁ ሥልጣን ያዙ። እንዳልኩት ግለማየሁ እምነበት ይሁን ሌሎች አይለውበት ባላውቅም የኛን አቋም እያወቀ በመኢሶን፣ በሕዝብ ድርጅት፣ በቀበሌና በፋብሪካዎች ላይ የተያዘው ዘመቻ እያየለ መጣ። የተከተለው ጥር ወር በተለይ ለኛ ወጣቶች እጅግ አስከፊ ወር ነበር። የመኢሶን አመራር ወይ ተደራድሮ የግድያውን ዘመቻ አላቆመላቸው፣ ወይ ደግሞ ራሳቸውን የሚከላከሉበት መሣሪያ አላስታጠቃቸው። በዚህ ላይ ደርግ በጸረ መኢሶን ኃይሎች ቁጥጥር ስር ወደቀ። ሕዝብ ድርጅትም፣ ቀበሌዎችም፣ ወዛደሮችም በጸረ ደርግ አቋም ተሰለፉ። ይህ ሰፈር በኢህአፓና በነግለማየሁ ላይ ያለው ጥላቻ ለማይ ነካ። ሁኔታውን ለድርድር ለማመቻቸት እነግለማየሁ ቢያንስ የግድያውን ዘመቻ ጋብ እንዲያደርግ መሞከር ሲችሉ ይባስ ብለው እንዲፋፋም አደረጉ። በዚህ ሁኔታ እኛም ደጋፊዎቻችንም ከነኢህአፓ ጋር የመደራደር ሃሳብ ጨርሶ ሊኖረን አልቻለም። ትጥቅና ዲሞክራሲን አፍነው ግድያውን በሚያግዙት በነግለማየሁና በደርግ ላይ ተቃውሟቸው ተጠናከረ። ይህ ደግሞ ተሸንፈው ተስፋ ቆርጠው ለነበሩት ኩሎኔል መንግሥቱ ረዳ። ጥር 22 ቀን በተደረገው ግማሽ ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ የተገኘበት ሰልፍ ላይ ሕዝቡ «አስታጥቀን» ከሚለው ጩኸት ሌላ መፈክርም አልነበረውም። በዚህ ሁኔታ ጄኔራል ተፈሪ በንቲ ከኢህአፓ ጋር ደርግ መቀራረቡን የሚጠቁም ንግግር ሲያደርጉና በእውነቱ ከልባቸው «ልጆቼ ለዚች አገር ስትሉ ተባበሩ» በሚል መንፈስ ያደረጉትን ንግግር ሰው እስከመጨረሻውም አላዳመጣቸው። ገና ሳይጨርሱ አደባባዩን እየለቀቀ መውጣት ጀመረ።

በዚያን ሰሞን በነበረው ሁኔታ ከነግለማየሁና ከደርግ ጋር ብሎም ከኢህአፓ ጋር የመቀራረብ ፖሊቲካ መከተል ይቻል አይቻል እንደነበረ በእውነቱ አሁንም መናገር ያቅተኛል። ግን ደግሞ አንድ የምገነዘበው ነገር አለ። ይህ ደግሞ አንድ ያመለጠ የታሪክ አጋጣሚ እንደሆነ ይሰማኛል። እስካሁን የምንከራከርበት ነጥብ ነው። አንዳንዶቻችን ያን ጊዜ በይፋ ለኢህአፓ የድርድር ጥሪ ማድረግ፣ የጄኔራሉን ጥሪ በይፋ ተቀብሎ መንቀሳቀስ ይቻል ነበር እንላለን። ሌሎቻችን ይህንን ጥሪ ያኔ ብናስተላልፍ ኢህአፓ ሆነ እነ ግለማየሁ የድካም ምልክት አድርገው ከመቁጠርና ንቆ ችላ ከማለት አይመለሱም የሚል ነበር። ዞሮ ዞሮ በኛ ወገን የተሰለፈው ኃይል አይገባውም ነበር። ከሁሉም በላይ ደግሞ በጥር 22ቱ ሰልፍ በነግለማየሁ ላይ የነበረውን ጥላቻ በማየት ሞራላቸው እጅግ ከፍ ያለው ኩሎኔል መንግሥቱ እነግለማየሁን ተሸቀዳድመው ከመገልበጥ አይታገዱም ነበር እንላለን። ይህ ክርክር የተከሰተው ግን በኋላ ነው። ያኔ ያሰበውም የለ።

ለማንኛውም ከዚያ በኋላ የመኢሶን አመራር አንድ የተገነዘበው ጉዳይ ቢኖር ይህንን የግድያ ዘመቻ ከማቆም አንጻር ከደርግ ምንም ነገር መጠበቅ እንደማይቻል ነው። የጄኔራል ተፈሪ በንቲ ንግግር እንኳን ዝም ብሎ ታሪክ ከማለት ይልቅ በይፋ ኢህአፓ የግድያ ዘመቻውን በማውገዝ እንዲያቆም ቢጠይቅ ኖሮ ምናልባት ትንሽ ተስፋ ያለው ሁኔታ ይኖር ነበር። ግን ይህንን አላሉም። ሁኔታዎች ግልጽ ከሆኑ በኋላ መኢሶን ባለችው አቅም ቢያንስ በኃይል የተጋለጡትን አባላቱን ለመከላከል ውሳኔ አደረገ። መሣሪያ በተቻለ ማስታጠቅ። ግን ደግሞ ያን ሁሉ የተጋለጠ ታጋይ ለማስታጠቅ አቅሙ የለም። በመኪና የምንሄደውና ከሁሉም በላይ ደግሞ አልታጠቅም ብለን የማንጠረጠረው ሰዎች ያለንን ሻል ያለ መሣሪያ እንድንፈታና በርግጥ አደጋ ላይ ያሉት ወጣቶች እንዲታጠቁ ከመወሰን ሌላ አማራጭ አልነበረንም። በጥር ወር የተደረገውም ይኸው ነው።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጥር 25 ቀን ተካሄደ የተባለው «እልቂት» የተፈጸመው በዚህ የፖለቲካ ሁኔታ ነበር። ነገደ ጉበዜ የመኢሶን ኩማንደ እየመራ ተማሪዎች የተሰበሰቡበት አዳራሽ በድንገት ደርሶ ሰው ፈጀ የተባለበት ተረት ነው። ተረት የምለው ሆን ብየ ነው። የዚያን ለት እኔ በቦታውም አልነበርኩም። እኔ ሪፖርቱን ባላይም በኋላ እስከሰማሁት «እልቂ» የተባለው ፈጠራ ነው። አንድም ተማሪ የሞተ አልነበረም። የቆሰለው አራት ተማሪ ነው። የዚያን ለት የሞተ ተማሪ አለ ከተባለ ለመታረም ዝግጁ ነኝ። ከሁሉም በላይ ደግሞ እዛ የነበረ ሁሉ እንደሚያስታውሰው ተኩስ መጀመሪያ ረድፍ ተቀምጠው በነበሩ በኛው ልጆች ተጀመረ እንጂ ባቢሊ ቶላ የተባለ «ቱ ኪል አ ጄኔራሽን» የተባለውን ተረት የጻፈ ሰው እንዳለው ከውጭ በድንገት ደርሶ ተኩስ የከፈተ ኩማንዶ አልነበረም። ለዚያውም እንግዲህ በዚህ ቀን የመኢሶን አመራር ይህ ርምጃ እንዲወሰድ ሲወስን ግልጽ የሆነ የፖለቲካ መልእክት ለነግለማየሁም ለኢህአፓዎችም ለማስተላለፍ እንጂ «ሰው ለመጨረስ» አልነበረም።

ተኩሱ ቢያንስ አስር ደቂቃ ያህል ቆይቷል። አራት ሰው ሲቆስል ሰው ያላለቀበት ምክንያት ግልጽ ነው። የተሰጠው መመሪያ ወደሰማይ ብቻ እንዲተኩስ ነበር። ሰዎች የመቁሰላቸው ምክንያት አንዳንድ የኛ ወጣቶች ከመመሪያ ውጭ በሰው ላይ ተኩሰው ይሆን ወይስ ከኢህአፓዎች በኩል የመጣ ተኩስ ይሁን መናገር ይቸግረኛል። ለኛ ግን ዋናው ነገር በዚያን እለት ያ ሁሉ ተኩስ ተካሂዶ ሰው አለመሞቱ ነው። የዚህ ርምጃ የፖለቲካ መልዕክት ግልጽ ነበር። ለአምስት ወር ያህል መኢሶን ከፍ ብየ በጠቀስኳቸው የአቅምና የፖለቲካ ምክንያቶች የራሱን ኩማንዶ አቋቁሞ በግለሰብ ግድያ አልተሰማራም ነበር። ጥር 25 ቀን ያንን ርምጃ የወሰደው ከእንግዲህ በየትምህርት ቤቱ በዚያን ሰሞን የተስፋፋው ግድያ ማቆም እንዳለበት፣ ካለቆመ ደግሞ መኢሶን ምንም እንኳን ደርግ ትጥቅ ቢነሳውም፣ ባለው አቅም ከእንግዲህ ራሱን ለመከላከል እንደወሰነ ለሚመለከታቸው ሁሉ ለማስጨበጥ ነበር።

ለማንኛውም በማግሥቱ ጥር 26 ቀን ኩሎኔል መንግሥቱ በነግለማየሁ ላይ መፈንቅለ መንግሥት አደረጉ። ይህ ደግሞ ራሱን የቻለ ሌላ ታሪክ ነው። የዚያን ለት የተገለበጡት እነግለማየሁ ብቻ አይደሉም። ደርግም ነው

ያከተመለት። ከአንድ ወር በፊት ኩለኔል መንግሥቱን ከሥልጣን አውርደው፣ ለነገለማየሁ አስረክበው እየተሾሙ በየክፍለ ሀገራት የተሰማሩትን የደርግ አባላት ማየት ነበር ያኔ። ለመግለጽ ቃል አላገኘለትም። በልዩ አውሮፕላንም፣ በመኪናም እየተሽቀዳደሙ የእለቱ ዕለትም በማግስቱም እየመጡ እጃቸውን ለኩለኔሉ ሰጡ። የሚያሳዝንም፣ የሚያሳርፍም፣ የሚያስቅም ትርዒት ነበር። የዚያኑ ያህል ደግሞ በመኢሶንና በህዝብ ድርጅት እንዲሁም በህዝባዊ ድርጅቶች ላይ ያላቸው ጥላቻ ለማይነካ ማለት ይቻላል። ይህ ደግሞ ለሚመጡት ወራት ሁኔታዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው ወዲያውኑ መስመር ያለበት ከስተት ነበር።

ይህ መፈንቅለ መንግሥት በ1969 ዓ.ም የሽብር ሂደት ሌላ አጭር ምዕራፍ ከፍቷል። ሁለተኛው ወቅት መሆኑ ነው፣ የካቲትና መጋቢት 1969 ዓ.ም። መኢሶንና ቀበሌዎች በዚያን ጊዜ በነበረው አባባል «ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት» የተሸጋገሩባቸው ወራት ናቸው። ቀደም ሲል መቋቋም የጀመሩትና የፖለቲካ ንቃት ስለሰጣቸው፣ በጠመንጃ ሳይሆን በዱላ ትጥቅ የውትድርና ልምምድ ያደርጉ የነበሩት በየቀበሌውና ፋብሪካው የተቋቋሙት የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች ትጥቅ ተሰጣቸው። ያውም ደግሞ ሁሉም አይደሉም። እኔ እስከማስታውሰው ድረስ ለምሳሌ አዲስ አበባ ከነበሩት 291 ቀበሌዎች መጀመሪያ ላይ ትጥቅ የተሰጣቸው 44ቱ ብቻ ነበሩ።

ካለፉት አምስት ወራትና ከሚቀጥለው ወቅት በተለይ ደግሞ ከ1970ው አስቃቂ ሁኔታ ጋር ሲነጻጸሩ እነዚህ የመኢሶንና የሱ ደጋፊ የሆኑት የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች የአጥቂነት የሁለት ወራት ወቅት ብዙ ደም ፈሰሰባቸው የሚባልላቸው ወራት አይደሉም። «አብዮታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ይሸጋገር» ስንል ለዚህ መፈክራችን ስንተነው የነበረው ትርጉም ራሱ የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴ በምሳሌነት ከተወሰደበት ከኩባ አብዮት ሁኔታ ትምህርት ተስመን ነበር። በየቀበሌው፣ በየፋብሪካው፣ በየትምህርት ቤቱ ያሉና በግድያ ሊሰማሩ ይችላሉ ተብለው የሚጠረጠሩ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ይዋሉ የሚል ጥያቄ ነበር። በዚህ መሠረት በያለበት የሚጠረጠሩ ሁሉ እየተያዙ ለፖሊስ ተሰጥተዋል። አንዳንድ ጊዜ በተኩስ ልውውጥ ሌላ ጊዜ ደግሞ አሳስፈላጊ የሆኑ ግድያዎች በዚህ ወቅት ተፈጽመዋል። ዋናው ነገር ግን በዚህ ወቅት እነዚህን ወራት በእውነቱ «ደም የጠማቸው ወራቶች» ማለት አይቻልም።

እርግጥ በዚህ ወቅት የገርማ ከበደ በጊዜው ሀገሪቱን እጅግ ያስቆቆ ግፍ ተፈጽሟል። 9 ሰዎች፣ ከነሱም መሀል አንዲት የስምንት ወር እርጉዝ የነበረች የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኛ በግፍ ረሽና ሬሳቸውን መንገድ ላይ እንዲጣሉ አድርጓል። ይህ ሰው የነለገሠ አስፋው ምልምል እንጂ በምንም ዓይነት የመኢሶን አባል ሆኖም አያውቅም። ተይዞ ሲመረመር በማን ግፊት እንደሆነ አላውቅም መጀመሪያ የመኢሶን አባል ነኝ ብሎ ነበር። ኩለኔል መንግሥቱ ጠርተው እንዲህ ይላል ብለውኝ ጨርሶ አስተባብየ እንደነበረ ትዝ ይለኛል። የሆነ ሆኖ በኋላ ገርማ ከበደ ራሱ ደጋፊ እንጂ አባል አይደለሁም ብሏል፣ በምርመራው ጊዜ። ግን ይኸ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ነው፣ የመኢሶን አባል መሆን አለመሆኑ። የፈጸመው ግፍ ወደር የማይገኝለት ነበር።

ሰው እንዴት ልብ እንዳላለው ጨርሶ ሊገባኝ ባይችለኝ ከዚህ እኮ ማንም የማያመልጠውና በ1969 ዓ.ም የነበረውን ሁኔታ ለመገንዘብ የሚያስችል መደምደሚያ አለ። ገርማ ከበደ በዚያን ጊዜ የፈጸመው ወንጀል በጊዜው ከነበረው ሁኔታ ጋር ጨርሶ የማይሄድ ወንጀል ነበር። አስቃቂና የተለየ ድርጊት ነበር። ለዚህም ነው ወዲያው በሞት ፍርድ የተቀጣው። በኋላ በ1970 ዓ.ም በሺ የሚቆጠሩ ገርማ ከበደዎች ፈልተው ነበር፣ በደርግና በሰደድ አይሂችሁ እየተባሉ። መኢሶን የበላይነቱን ይዞ በነበረባቸው በየካቲትና መጋቢት 1969 ዓ.ም ግን እንኳን ለሺህ ገርማ ከበደዎች ለሁለትም ቦታ አለነበረም። የመኢሶን ጠላቶች በኋላ ደግሞ ገርማ ከበደ በመረሸኑ የመኢሶን አመራር ለደርግ ተቃውሞውን አሰምቷል ብለዋል። ነገሩ በደንብ ስለማውቀው ይህንን ላብራራ እችላለሁ። ዶክተር ከበደ ልኩኝ ለኩለኔል መንግሥቱ ተቃውሞና ቅሬታ አሰምቻለሁ። ግን ይህ ተቃውሞና ቅሬታ የሚመለከተው በገርማ ከበደ ላይ የተወሰደውን ርምጃ ሳይሆን ይህንን እርምጃ አስታኮ በወጣውና በገርማ ከበደ ሳቢያ በጠቅላላው ቀበሌዎችን የደም ጥመኞች አድርጎ ያቀረበውን የደርግ መግለጫ ይዘት ነበር።

የሆነ ሆኖ ይህ የአጥቂነት ዘመን የብዙ እሥራት እንጂ የደም ጉርፍ ዘመን አልነበረም። የዚህ አጥቂነት አንዱ መልኩ የትጥቅ ማስፈታት ዘመቻ ነበር። ሁለት አሰሳዎች ተካሂደዋል። የተካሄዱትም በሥነሥርዓት ነው። ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይና ከኢህአፓ መሪዎች ማርቆስ ሐጉስ በነዚህ አሰሳዎች ጊዜ ሞተዋል። ሌሎችም ~~ቁጥራቸው 5 ይሁን~~ ሰባት አላስታውስም፣ የኢህአፓ ወጣቶች ከቀበሌዎችና ከሌሎች በአሰሳው ከተሰማሩ ወታደሮችና የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ታጋዮች ጋር ባደረጉት የተኩስ ልውውጥ ህይወታቸው አልፏል።

ይህም ወቅት ብዙ አልቆየም፣ የሁለት ወር እድሜ ነበረው። ከመጋቢት መጨረሻ ጀምሮ የኛ ሰፈር እንደገና ወደተከላካይነት ገባ። በሚቀጥሉት ወራት የሚወጡትን የጋዜጣችንን «የሰፊው ህዝብ ድምጽ» ቁጥሮችን ማየት ይበቃል። በተከተሉት ወራት ስለነበረው የኛ የተከላካይነት ሁኔታ በመብሸትና በመመረር የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤትን «የቀብር አደራጅ ጽ/ቤት» እያልን መጥራት የጀመርንበት ወቅት ነበር። መጋቢት መጨረሻ ለኛ ሌላ ምእራፍ የከፈትንበት ወቅት ነበር። ከደርግ ጋር የነበረን ግንኙነት እንዳለተ ገምግመን፣ ከየክፍለ ሀገራቱ የድርጅቱ መሪዎች በተገኙበት ምስጢራዊ ብሔራዊ ጉባዔ በመጥራት ህቡዕ ለመግባት ዝግጅት እንዲደረግ የወሰንንበት ጊዜ ነው።

የመኢሶንና የህዝብ ድርጅት እንዲሁም የቀበሌዎችና የወዛደር ኩሚቴዎች ወደተከላከይነት መውረድና የታጋዮቻችን እንደገና ማለቅ የመጣው የፖለቲካው ሁኔታና የኃይሉች አሰላለፍ በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ በመቀየሩ ነበር። የዚህ ታሪክ ረኻርምም ቢሆን ይዘቱ ቀላል ነው። የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች እየተባሉ በቀበሌም፣ በየፋብሪካውም ትጥቅ በመታደል ላይ ያሉት አበዛኞቹ የመኢሶን አባላትና ደጋፊዎች እንደሆኑ ለመረዳት ኩለኔል መንግሥቱም ሆኑ ሰደዶች ምንም ጊዜ አልወሰደባቸው በገጠርም ሆነ በከተማ ህዝብን በማደራጀት ከሁሉም በላይ የተሰማራው ድርጅት በዚያን ወቅት መኢሶን ነበርና። መኢሶንን መቆጣጠር ስለማይችሉ የነበራቸው ምርጫ እምብዛም አልነበረም። በገለማየሁ ወገን የነበረውንና በነሱ መወገድ ትስሙ የተሰበረውን ቢሮክራሲ፣ ፖሊስ፣ የደርግ አባል መወዳጀትና መኢሶን ህዝብ ድርጅትንና ህዝባዊ ድርጅቶችን መዋጋት ነበር። ከመጋቢት ጀምሮ መታየት የጀመረው ይህ ጸረ መኢሶን ህብረት ነበር። አብዮታችንንም ይዞ ገደል የገባው ይህ ጸረ አብዮትና ጸረ ዲሞክራሲ ሽርክና ነበር። በዚያን ጊዜ እንለው በነበረው አባባል በዚህ ወቅት «አዲስ የቆኞች አልያንስ» የሚባለው ተጀመረ። ከዚያስ ምን ሆነ? በሚቀጥለው እትም እናየዋለን። □